*የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)*
*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

ህዳር 12 ቀን 2011 ዓ.ም.

## <u>የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)</u>
## ስድስተኛው የፓርቲ ጉባዔ
## <u>ጋዜጣዊ መግለጫ</u>

ስድስተኛ ጠቅላላ ጉባዔውን፤ ከኅዳር 6 እሰከ ኅዳር 8 2011 ዓም ባሉት ቀናት ውስጥ አካሄዶ በስኬት አጠናቅቋል። በጉባዔ ከአራቱም የአለም ማዕዘናት ተወክለው የተገኙ አባላት ተካፍለዋል። የጉባዔው ተሳታፊዎች ፤ ከፓርቲው ከፍተኛ አማራር ኮሚቴ የቀረበውን የሥራ ዘገባ ( ሪፖርት) አዳምጠው ሰፊ ውይይትና ክርክር ከአካሄዱ በኋላ በሙሉ ድምፅ አጽድቀውታል።

በፓርቲው ፕሮግራም፤ የውስጥ ደንብ እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎች አድርጓል። የፓርቲው ድርጅታዊ መዋቅር እና እንቅስቃሴ እንዲጠናከር በተጨማሪም የወጣቶችና የሴቶች ተሳትፎ የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ውሳኔ አስተላልፎ ለአመራሩ መመሪያ ሰጥቷል ።
ይህ ጉባዔ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የአብሮ መኖር ኅልውናም ሆነ የዴሞክራሲ መብት ጉዳይ፤ ለድርድር የሚቀርብ እንዳልሆነ በድጋሚ አስረግጧል። በዲፕሎማሲ መስክ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ጉባዔው ውሳኔ ያስተላለፈ ሲሆን፤ ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ትግልን የማስተባበር ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ እንዲሆን ጉባዔው አጽንኦት ሰጥቶ ውሳኔ አስተላልፏል ።

ለአመታት ሕዝባችንን ከባድ መሥዋዕት የከፈለበትን የሰብዓዊ መብቶች መከበርና የአንድነት መኖር ትግል፤ ግቡን እንዳይመታ በወያኔና በባዕዳን የሚደረገውን ሴራ ማክሸፍ ብርቱ ትግልን እንደሚጠይቅ ተገንዝቦ፤ አመራሩ ሁኔታውን እየተከታተለና እየገመገመ አስፈላጊ ዕርምጃዎችን ተግባራዊ እንዲያደርግ መመሪያ ሰጥቷል። በመሆኑም፤ ሳይዘናጉ መከታተል አስፈላጊ መሆኑን አምኖበታል።

የኢሕአፓ ስድስተኛ ጉባዔ፤ የሀገራችን ፖለቲካዊ፤ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕውነታዎችን ከዓለምአቀፍ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ አጠቃላይ በሆነ መልኩ ግንዛቤ ወስዶና ገምግሞ ሥር ነቀል የሥርዓት ለውጥ ለማምጣትና ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት የሚሆንበትን ሁኔታ ለመፍጠር ትግሉን ከማጧጧፍ ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለ አምኗል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ለአመታት የታገለለትን የሕዝባዊ መንግሥትና ዴሞራሲያዊ ጥያቄ ግቡን እንዳይመታ ፤ በባዕዳን ተኮትኩቶ ያደገው የአገዛዙ ሹም፤ ተቃዋሚ ኃይሎችንና ሌሎችም የኅብረተስብ ክፍሎች በማግለል፤ " እኔ ላሸጋግራችሁ " በማለት ትግሉን ለመቀልበስ የሚያደርጋቸውን ጥረቶች ጉባዔው ተገንዝቧል። ባዕዳን ኃይሎች ፤ የሀገራችንን ሀገራዊ ጥቅም በመጋፋት ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ በሥልጣን ላይ

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website [www.eprp.com](http://www.eprp.com)**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

ያለውን አገዛዝ ጠጋግኖ፤ የሕዝባችንን ትግል ለማደናቀፍ የሚያደርጉትን ሴራ በጥልቀት መርምሯል ። ሕዝባችን የሥልጣኑ ባለቤት ለመሆን የሚያበቃውን የሽግግር ሂደት ዕውን እስከሚሆን ድረስ ትግሉን አፋፍሞ መቀጠል እንዳለበትም ወስኗል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአስመሳዮች ሳይዘናጋ፤ ለዘላቂ ድል ትግሉን እንዲቀጥል ጥሪ አቅርቧል።

በመጨረሻም ፤ ጉባኤው ለሚቀጥለው የትግል ዘመን የሚያገለግሉ የፓርቲ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባላትን በመምረጥ፤ ስብሰባውን በተሳካ ሁኔታ አጣናቅቋል ።

ለማይቀረው ሕዝባዊ ድል ትግላችንን እናፋፍም!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር !